## ለሁሉም የ Diaspora outreach ኮሚቴ አባላት በሙሉ!

ዶ/ር ዐብይ በአሜሪካ ለሚያደርጉት ጉብኝ አቀባበል ዝግጅቱ በሎስ አንጀለሰና በሁሉም ትላልቅ ከተሞች የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ተዋቅረው እየተንቀሳቀሱ እንዳሉ ይታወቃል::

እነዚህ ኮሚቴዎች የተዋቀሩት ክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡ ወዲህ የተገኙትን ለውጦች ለመደገፍ; ከጎናቸው ለመቆም ብሎም መደመር የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያ በሙሉ ያለምንም የብሔር; የእምነት; የፖለቲካ አመለካከት; የጾታ; የሃብት ; ወዘተ... ልዩነት ሳይደረግ ወደ ጉባኤው ለመምጣት የሚፈልጉ ሁሉ መልእክቱን እንዲያስተላልፉ አላማ አድርገው የተሰየሙ የተቋቋሙ ናቸው::

ይህ ማለት ግን ወደ ጉባኤው ሊመጣ ያሰበ ሰው ሁሉ የግድ በነዚህ ኮሚቴዎች ስር ማለፍ ወይም መመዝገብ አለበት ማለት አይደለም:: የእነዚህ ኮሚቴ አባላት ተግባር በዋናነት "ኢትዮጵያ" እንደ አገር ለዜጎችዋ ያደረገችውን አገራዊ ጥሪ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በቡድን ወይም በተናጥል ማስተላለፍ ነው:: እግረ- መንገዳቸውን ስንት ሰው በተጨባጭ ሊገኝ እንደሚችል ሰው አስቀድሞ በonline ወይም በተዘጋጁ ሠንጠረዦች ( ወደፊት አብይ ኮሚቴው በሚያስቀምጠው የምዝገባ አቅጣጫ) እንዲፈጸም ላልሰሙት ማሰማት ነው::

ስለዚህ አሁን ያለው አቅጣጫ ማንንም ከማንም ሳይለይ በጉባኤው ላይ ለመገኘት አዳራሹ እስከቻለ ድረስ መሳተፍ እንደሚችል ሁሉ በተለይም ማህበረሰቡን ለማነሳሳት በየቦታው በሚዋቀሩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ውስጥ በግልም ይሁን በቡድን በመሳተፍ የድርሻቸውን ለማበርከት ፍላጎት ያላቸው ሁሉ ያለ አንዳች ገደብ እንዲሳተፉ በአክብሮት እየጠየቅን; በዋናነት በየከተማው ያሉ የተለያዩ የኢትዮጵያውያን አደረጃጀት ( የኮሚኒቲ; የልማት; የባለሙያዎች; የስፖርት; ወዘተ እና የተለያዩ ስብስቦች ( የእቁብ; የእድር; የጹዋ ወዘተ.. ) መሪዎች; የተለያዩ የእምነት ተቋማት መሪዎች; ካሁን ቀደም የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ቡድኖች መሪዎች; የወጣት; የሴቶች አደረጃጀቶች; በአሜሪካን ኮንግረስና ሴኔት ውስጥ ተመራጭ የሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን; በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ መያዶች ( NGO) ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ባለሙያዎች; በየአካባቢው የሚኖሩ ታዋቂ ግለሰቦች; ወዘተ..በኮሚቴው ውስጥ እንዲሳተፉ በመገፋፋት በሚመሩዋቸው ድርጅቶችና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ዜጎቻችንን እንዲያነሳሱ ታደርጉ ዘንድ በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን::

ይህን ፅሁፍ ሁላችሁም ለሌሎች ሰዎች forward በማድረግ ተባበሩን::

"ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦችዋን ይባርክ !!"

ከሎስ አንጀለስ የዳያስፖራ ተሳትፎ ንዑስ ኮሚቴ

*Sincerely !*

Tafa Tulu Dadi

Minister Counseler

(Head of Diaspora Affairs)

Telephone # +1213 365 6651 Ext. 117
Fax # +1213 365 6670
Mobile # +1323-690-0003